DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

ውድ የዲሲፒኤስ ትምህርት ቤቶች ወላጆች፣

ዲሲፒኤስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች(DCPS)፣ እያንዳንዱ ልጅ የሚወደድበት፣ በጥንካሬ የሚጎለብትበት፣ እና ማኅበረሰቡ በሕይወት እንዲጥር እና የታታሪነት ዝንባሌ የሚያሳድር እንዲሆን የሚዘጋጅበት ነው። እያንዳንዱ የ 2018 እጩ ተመራቂ ተማሪ ዲፕሎማ ለመቀዳጀት ዝግጁ እንዲሆን እውን ለማደረግ በመካሄድ ላይ ባለው ጥረታችን፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ የከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ማስረጃዎችን በመመርመር እና እያንዳንዱ ተማሪ እና ወላጆቻቸው ለመመ ረቅ የሚያበቋቸውን ሂደቶች እንዲገነዘቡ ለማድረግ፣ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው በእያንዳንዱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተምህርት ቤት፣ የትምህርት ድጋፍ ሰጪ ግብአቶች መታያ ኤግዚቢሽን ያካሂዳል።

ከንቲባ ሙሪል ባውዘር (Muriel Bowser)፣ ጊዜያዊ ተጠባባቂ ቻንስለር ዶክተር አማንዳ አሌክሳንደር (Dr. Amanda Alexander)፣ ምክትል ተጠባባቂ አህና ስሚዝ (Ahnna Smith) በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የትምህርት ግብአቶች መታያ ኤግዚቢሽን ለማካሄድ የዲስትሪክት ወኪሎችን እና አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አንድ ላይ እያቀራረበ ነው። የትምህርት ግብአቶች መታያ ትርኢቶች፣ ስለ በጋ የእረፍት ወቅት ሥራዎች፣ ስለመኖሪያ ቤቶች ችግ ሮች ጉዳይ፣ የሕጻናት ጥበቃ፣ መጓጓዣዎች እና ስለ ሌሎች የከተማ አገልግሎቶች ለተማሪዎች እና ለወላጆቻቸው ሊገኙ ስለሚችሉባቸው ጉዳዮች መረጃዎችን ያቀ ርባል። የትምህርት ድጋፍ ሰጪ ግብአቶች መታያ ዝግጅቶች ከዚህ በታች በተመለከቱት ቦታዎች እና ቀናት የሚካሄዱ ይሆናል።

- Wilson ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 2፣ ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- Dunbar ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 7, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- H.D. Woodson ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 9, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- Coolidge ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 14, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- Anacostia ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 16, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- Eastern ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ መጋቢት (March) 21, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም
- Cardozo Education Campus: መጋቢት (March) 23, ከ 3:30 — 5:30 ፒኤም

ለ 2017-2018 የትምህርት ዓመት፣ በትምህርት ገበታ ላይ ስለመገኘት እና የተማሪዎች የትምህርት አከናወን ፖሊሲዎችን በሚመለከት፣ እባክዎን የ **2018 የ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ላይ ስለ መገኘት እና ተማሪዎች የወደቁባቸውን ትምህሮቶች ውጤቶች ስለሚሟላት ተዘውትረው የሚነሡ ጥያቄዎች ጉዳይ ለወላጆች (2018 High School Attendance, Grading, and Credit Recovery FAQ For Fami- lies)** በ https://dcps.dc.gov/graduation. ላይ ይገኛል። ይህ ሠነድ ከተርም 2 (Term 2) ተማሪዎች ያለፈቃድ ከትምህርት ገበታ በመቅረት ምክ ንያት የተነሣ ዝቅተኛ ውጤቶች ስላመጡባቸው ወይንም ስለ ወደቁባቸው ትምህርቶች፣ ተማሪዎች እና ወላጆች አቤት ማለት ስለሚችሉባቸው ሂደቶች ጭምር በጣም ጠቃሚ መረጃዎችን ይይዛል። እባክዎን በዚህ ማብራሪያ **ምክንያት፣** **የትምህርት ውጤት የመቀነስን እና የመውደቅን በይግባኝ አቤቱታ ጉዳይ የተነሣ ዲሲ ፒኤስ ቀኑን ወደ ዓርብ መጋቢት (March) 9 አራዝሞታል።** ወቅቱን የጠበቀ እንዲሆን ተደርጎ የቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ቅጽ በ https://dcps.dc.gov/ graduation. ላይ ይገኛል።

እንደ ምረቃ ማረጋገጫ አካል፣ ዲሲፒኤስ (DCPS) ለመመረቅ በዝግጅት ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን የትምህርት ውጤት ማስረጃዎች ሁሉ የማጣሪያ ምርመራ እያካ ሄደ ነው። የትምህርት ውጤት ማስረጃዎች የማጣሪያ ምርመራ ተጣርተው እንዳበቁ፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና ወላጆች ስለተማሪዎች የምረቃ ደረጃ ሁኔታ መረጃዎች የደረሳቸው መሆኑን ያረጋግጣል። የ 2018 ክፍሎች የተመራቂ ቡድን አካል አባል ከሆንክ እና እስከ አሁንም ድረስ የተመራቂነት ሁኔታህን በሚ መለከት ከትምህርት ቤትህ ጋር የተነጋገርክ ካልሆንክ፣ እባክህን የትምህርት ቤትህን የተማሪዎች የትምህርት አማካሪውን አነጋገር።

የትምህርት ዓመቱን እያገባደድን በምንገኝበት ሰዓት፣ እያንዳንዱ ተማሪ፣ ወላጅ፣ እና የማኅበረሰብ አባል፣ ተመራቂ ተማሪዎቻችን ለኮሌጅ ትምህርት፣ ለሙያ እና ለሕይወት ዝግጁ መሆናቸውን በመረዳት ስለእድገት እርምጃዎቻችን ግልጽ መሆናችንን እንቀጥላለን። በዚህም፣ በሰኔ (June) ወይንም ነሀሴ (August) 2018 ለመመረቅ በያዝ ለቀቅ ሁኔታ ላይ የሚገኙ የዲሲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጨረሻ ክፍል ተማሪዎች ስንት መቶኛ እንደሆኑ የሚያመለክት የአጋማሽ ዓመት ወቅቱን የተከተለ መረጃ ዲሲፒኤስ እያቀረበ ነው። ስለ ተመራቂዎች መረጃ ጉዳይ እባክዎን https://dcps.dc.gov/graduation ን ይቃኙ።

ከአክብሮት እና ከከፍተኛ ግምት ጋር፣

Wanda H. Legrand, Ed.D.
Deputy Chancellor, Social Emotional Academic Development